NABU

PARTNERSHIP FOR LAKE TANA WATERSHED ETHIOPIA
WATER FOR LIFE

ውሃን በአግባቡ እንጠቀም!



ውሃ ህይወት ነው – መቆጠብ የእኛ ድርሻ ነው

„Water for Life - Partnership for a sustainable future of the Lake Tana Watershed, in Ethiopia“
Supported by the German Federal Ministry for Economic Cooperation and Development (BMZ)

german cooperation
DEUTSCHE ZUSAMMENARBEIT



Photo: Bruno d'Amicis, 2019

ውሃ ለህይወት- ተፈጥሮ ሀብትን ለመጠበቅና ለመንከባከብ የባህሪ ለውጥ ዘመቻ

በናቡ የተዘጋጀ በጣና ሃይቅ ተፋሰስ ተፈጥሮ ሀብትን ለመጠበቅና ለመንከባከብ የባህሪይ ለውጥ ዘመቻ

በጣና ሃይቅ እና ገባር ወንዞች ላይ የሚገኘውን ውሃ የኑሮ መሰረት በማድረግ አራት ሚሊዮን የሚገመት ህዝብ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ይኖራል። ነገር ግን በፍጥነት እያደገ ባለው የህዝብ ቁጥር፣ ትክክለኛ ያልሆኑ ቦታዎች ላይ የተወሰኑ እንዲስትሪዎች በመገንባታቸው ምክንያት፣ ምርታማነትን ለመጨመር ከመሰኖ እና ከሌሎች የግብርና ስራዎች መስፋፋት ጋር ተያይዞ ወደ ሀይቁ የሚገቡ ኬሚካሎች እየጨመሩ በመሄዳቸው እና የአፈር ክለት እየጨመረ በመሆኑ በተፋሰሱ ውስጥ ያለው ውሃ ሀብታችን አደጋ ላይ እየወደቀ ይገኛል። በዚህም የተነሳ የዓሳ ምርት በመቀነሱ፣ መጤ አረም እንደ እንቦጭ ያለ በመስፋፋቱ፣ የውሃ መጠኑና ጥራቱም እየቀነሰ በመምጣቱ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጉ በኢትዮጵያና በታችኛው የአባይ ተፋሰስ የሚገኙት ነዋሪዎች አደጋ ላይ ሊወድቁ እንደሚችሉ ይገመታል።

የውሃ ለህይወት ፕሮጀክት ዓላማዎች የባለድርሻ አካላት የትብብር መደረክ በማቋቋም እነዚህ የባለድርሻ አካላት በጋራ በመስራት በተፋሰሱ ውስጥ ዘላቂነት ያለው ንፅህ የውሃ አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ፣ ያልተገደበ የስነ-ምህዳር አገልግሎት ነዋሪዎች እንዲያገኙ ማስቻልና ዘላቂነት ያለው የገቢ አማራጭ የአካባቢው ማህበረሰብ እንዲያገኙ ማስቻል ናቸው።

በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱ ዓላማዎችን ለማሳካት የዋና ዋና ባለድርሻ አካላትን የባህሪይ ለውጥ ማምጣት እንደዋነኛ ስትራቴጂ በመያዙ በዚህ መሰረትም የአካባቢውን ማህበረሰብ፣ የሲቪክ ማህበራትን፣ በክልሉ ያሉ የመንግስት ተቋማትና ማዘጋጃ ቤቶችን፣ የሃይማኖት ተቋማትን፣ የንግዱን ማህበረሰብ፣ የምርምር እና የትምህርት ተቋማትን ለማካተት የታለመ ነው። ዘመቻው እነዚህን ባለድርሻ አካላት የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክባከቤ ላይ ግንዛቤን ለማሳደግ እና በተፋሰሱ ውስጥ በሚከናወኑ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራዎች ላይ አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት መነሳሳትን ለመፍጠር ነው።

ለባህሪ ለውጥ ዘመቻ የሚያገለግሉ ዘዴዎች እና መገናኛዎች

- ስልጠናዎች እና በወርክሾፖችን በመጠቀም
- ባነር፣ ፓስተር እና በራሪ ጹሁፎችን በመጠቀም
- ሬዲዮ እና ቲቪ በመጠቀም እና
- ደህረ ገፅች እና ማህበራዊ ሜዲያዎች በመጠቀም ነው።

PARTNERSHIP FOR LAKE TANA WATERSHED, ETHIOPIA
WATER FOR LIFE

ፕሮጀክቱ የሚገኝበት: ጣና ሃይቅ ተፋሰስ

ስፋት: 15.000 ስኳር ኪ/ሜ

በፕሮጀክቱ ቦታ የሚገኙ: ወደ 4 ሚሊዮን የሚጠጉ ነዋሪዎች

የሚካታቱ ወረዳዎች: 29

የሚካተቱ ቀበሌዎች: 429

በፕሮጀክቱ ቦታ የሚገኙ ትልልቅ ከተሞች: ባህር ዳር፣ ጎንደር እና ደብረታቦር

የባህሪይ ለውጥ ዘመቻው ዋና ዋና ዓላማዎች:

- የአካባቢ ጥበቃ ግንዛቤን ማሳደ
- በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ላይ ግለሰባዊ ሃላፊነትን ለመፍጠር
- በየሴክተሩ አካባቢን የማይጎዱ ተግባራት እንዲዘወተሩ ለማስቻል
- በተለያዩ ነባራዊ ሁኔታዎች እንደ ዘላቂ ልማት ፣ የካርቦን ልቀት ቅነሳ እና ወዘተ ያሉ ዘመናዊ ጽንሰ ሀሳቦችን ለመተግበር
- የአካባቢው ማህበረሰብ በተፈጥሮ ሀበት ጥበቃና እንክብካቤ ስራ ላይ በሬዲዮ እና በስልጠና በመታገዝ የውሳኔ ሰጪነት ሚናውን እንደጫወት ማበረታት ።

For further contact:
Lake.Tana@NABU.de
Lake Tana Biosphere Reserve

© 2021, The Nature and Biodiversity Conservation Union (NABU), Charitéstr. 3, 10117 Berlin, Germany, www.en.NABU.de